በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር

# የወቅት አጋማሽ የአየር ጠባይ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር1 እስከ ከኖቬምበር 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እና

## በቀሪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ እና ምክረ ሃሳብ

ዲሴምበር 2024

አዲስ አበባ



ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ


እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ የበጋ ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ ..... - 1 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ..... - 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ..... - 5 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ብዛት - 5 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2024 ድረስ ..... - 5 -

የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ..... - 5 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... - 6 -

ካርታ4ሀ፡በኦክቶበር ወር የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ ..... - 7 -

ካርታ4ለ፡በኖቬምበር ወር የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ ..... - 7 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... - 8 -

ካርታ5ሀ፡በኦክቶበር ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን ..... - 8 -

ካርታ 5ለ፡በኖቬምበር ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን ..... - 8 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... - 9 -

ካርታ 6ሀ. በኦክቶበር ወር ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች ..... - 9 -

ካርታ 6ለ በኖቬምበር ወር ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች ..... - 9 -

ካርታ 6ሐ. በኦክቶበር ለሰው ልጅ ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች ..... - 10 -

ካርታ 6መ. በኖቬምበር ወር ለሰውል ልጅ ለመኖር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች - 10 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2024 እስከ ጃንዋሪ 31/2025 የሚኖረው ..... - 10 -

የአየር ጠባይ አዝማሚያ ..... - 10 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2024 እስከ ጃንዋሪ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... - 11 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2024 እስከ ጃንዋሪ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... - 12 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2024 እስከ ጃንዋሪ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... - 12 -




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ የበጋ ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

## አጠቃላይ

ለዘንድሮ የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ ትንበያ ከመስጠቱ አስቀድሞ በትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ መካከለኛውና ምሥራቃዊ ክፍል ላይ ቀደም ባሉት ወራት የነበረውና በመጪዉ የበጋ ወቅት የሚኖረው የባህር ወለል ሙቀት ሂደት ላይ ሳይንሳዊ ትንታኔና ጥናት ተደርጓል፡፡ በበጋ ወራት የምስራቅና የመካከለኛዉ ፓስፊክ ዉቅያኖስ የላይኛዉ የዉሃ አካላት ከመደበኛው በታች መቀዝቀዝ (La Nina) ክስተት ተጽዕኖ ሥር ሆኖ እንደሚቀጥል በተጨማሪም የህንድ ዉቅያኖስ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ መሞቅ ጋር ተያይዞ የዘንድሮ የበጋው ወቅት (Neutral IOD) ስር ሊሆን እንደሚችል ተመላክቷል፡፡ በተጨማሪም በአትላንቲክ ውቅያኖስ ሰሜናዊ ክፍል እንዲሁም በሜዲትራኒያን ባህር ላይ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የባህር ወለል መሞቅ እንደሚኖር ተጠቁሟል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በመጪው በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረናና ጉጂ ዞኖች፣ ሲዳማ እና ደቡብ ኢትዮጵያ መደበኛ ዝናብ፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ክፍል ድግሞ ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠንና ስርጭት እንደሚኖራቸዉ ትንበያ ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም የምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ፣ በተጨማሪም እየተስተዋሉ ከሚገኙት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በሰሜን፣ በመካከለኛው፣ በምስራቅና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንደሚኖር በትንበያዉ ተመላክቶ ነበር፡፡

በዚህ መሰረት ባለፉት የበጋዉ ሁለት ወራት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች መበደኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል፡፡

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ባለፉት ሁለት የበጋ ወራት የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ ወራት ሊኖር የሚችለው የአየር ጠባይ አዝማሚያ እንዲሁም በግብርናው በዉሃ ሴክተሮች እና በጤና ላይ አሳድሮ የነበረው የዳሰሳ እንዲሁም ወደፊትም ሊፈጥር በሚችለው ተፅእኖ ላይ ጽሁፍ ቀርቧል።



ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፉት የበጋ ሁለት ወራት ወደ ሀገራችን ሲገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር ከመጠናከሩ ጋር ተያይዞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ ዝናብ በቦታና በመጠን ረገድ የተሻለ ነበር፡፡ እንዲሁም ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መጠናከር በማሣየታቸው ምክንያት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከነበራቸው የደመና ሽፋን በመጠንም ሆነ በስርጭት የተሻለ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላለ እስከ መከከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተስተውሏል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረዉ የደመና ክምችት የዝናቡ መጠንና ስርጭትም በተለያዩ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ የተመዘገበ ሲሆን፤ በጥቂት ቦታዎች ላይም ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡

በአጠቃላይ በኦክቶብር እና በኖቬምበር ወር ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢዎች ለመጥቀስም ያህል በአቦቦ 32.6፣ 30.8፣ በአልጌ 66.0፣ በአንገር ጉቲን 45.6፣ 30.6፣ 54.0፣ አዲግራት 55፣ አሊያ 49.1፣ በኢጃጂ 44.2፣ አማን 32.5፣ 39.4 ፣አሶሳ 32.2፣ 39.4፣ 43.8፣ በአዋሽ አርባ 40.0፣ 55፣ 60፣ በአዉራ መልካ 37.6፣ በእነዋሪ 38.5፣ በአርባ ምንጭ 31.8፣ 38.4፣ በአርጆ 32.6፣ 34.2፣ በአዋሮ 32.6፣ 34.2፣ በአፅቢ 33.4፣ በአይከል 32.5፣ በቡሬ 67.5፣ 57.0፣ በቡለን 30.2፣ 30.4፣ 30.4፣ ባህርዳር 54.2፣ ቡለን 30.5፣ በባቱ 33.2፣ በዱብቲ 51.2፣ ደባርቅ 35፣ በዳንግላ 48.2፣ በደብረ ታቦር 40.7፣ በበደሌ 33.7፣ ቻግኒ 37.1፣ 32.6፣ ጭራ 44፣ 30.2፣ 30.9፣ 37.9 በጭሮ 42.4፣ በጭፍራ 40.0፣ ቢሾፍቱ 33.8፣ 33.8፣ በፉኚዶ 73.6 እና 49.1፤ ጋምቤላ 38፣ 31.3፣ ጊዲ አያና 39.7፣ 56.1፣ ጊኒር 64፣ 75.6 ፣ጎሬ 47.2፣ 31.3፣ በግራዋ 35.7፣ በጉብሬ 46.2፣ በጉሊና 45.0፣ በጋቲራ 31.6፣ በጎዴ 30.8፣ በገርቦ 30.4፣ በጃራ 30.4በሀረር 52.0፣ 37፣ በቁሉቢ 36.9፣ በሐሮሚያ 33.0፣ በላሬ 50፣ 42.0፣ ሊሙ ገነት 35.5፣ 44.6፣ በማጂ 84.3፣ በማንኩሽ 52.0 እና 84.6፣ በማሻ 44.5፣ 30.1፣ መኢሶ 34፣ መተሐራ 58.1፣ 78.5፣ ሞጣ 34፣ በሞያሌ 46.0፣ በመተማ 39.3፣ በምዕራብ አባያ 31.0፣ በአምቦ 36፣ በንፋስ መዉጪያ 36.3፣ ነገሌ 36.1፣ ነቀምቴ 33፣ ኑራ ኤራ 51.9፣ በፓዌ 45.4፣ 40.6 እና 47.2፣ በሳዉላ 53.0፣ ቲፒ 33.4፣ በተርጫ 32.2፣ በሾላ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ገቢያ 43.3፣ በሸርቆሌ 48.6፣ በሽላቦ 65.0፣ በሽሬ 30.2፣ በጅማ 42.2፣ በሆሳዕና 40.7፣ 45፣ እንዲሁም ኮንሶ 42፣ 31.5፣ በካራሚሌ 34፣ በወሊሶ 31.2፣ እንዲሁም ወራቤ 96.0 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

በሌላ በኩል የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ እምብዛም ያልተጠናከረ ቢሆንም፤ በኖቬምበር ወር በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም በቢሾፍቱ 4.5፣ 2.0 እና 4.8፣ በአዲግራት 4.0፣ በሃሮማያ 3.8፣ 3.6፣ እና 4.2፣ በአለም ከተማ 4.8፣ 4.5 እና 3.4፣ በአምባ ማርያም 4.6፣ 3.4፣ 3.4፣ 4፣ 4.6፣ 4.6፣ 4.0፣ 2፣ 3.6፣ 4፣ 4.2፣ 4.4፣ 4.4፣ 4.8፣ እና 4፣ በአርሲ ሮቤ 4.5፣ 3.5፣ እና 4.5፣ በባቲ 4.6፣ በቡኢ 4.0፣ 4.6፣ 3.6፣ 3.6፣ 2.0፣ 2.6፣ 3.0፣ 4.6፣ 4.8፣ 4፣ 4.6 እና 4.6፣ በደባርቅ 5.0፣ በደብረ ብርሃን 4.0፣ 4.0፣ 4.6፣ -1.8፣ -0.2፣ 2.0፣ 4.8፣ 3.8፣ 3.2፣ 3፣ 3.6፣ 3.2፣ 4.2፣ 3. 4፣ እና 3.2፣ በእነዋሪ 2.5፣ 2.4፣ እና 2.5፣ በጅግጅጋ 1.5፣ 1.0፣ ፣1.4፣ 3.6፣ 4.8፣ 2.4፣ 2.4፣ 4.3፣ እና 3.6፣ በማይጨዉ 4.5፣ በመሀል ሜዳ 4.2፣ 0፣ 0.6፣ 4.8፣ 3.6፣ እና 3.2፣ በሾላ ገበያ 2.0፣ 2.0፣ 2.1፣ 4.0፣ 4.1፣ 2.1፣ 2.0፣ 3.0፣ 2.1፣ 2፣ 2.1፣ 2.1፣ 2፣ 2፣ 1.2፣ 2.1፣ እና 2 በወገል ጤና 4.8፣ 1.5፣ 2.0 2.4 እና 4.5፣ በወረኢሉ 4.2፣ እና 4.8 እንዲሁም በየትኖራ 4.8 በዲግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል፡፡

ባለፈዉ የበጋ ወቅት አጋማሽ የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሊ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች ከ101-400 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ17-35 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ከሶማሌ ክልል የሊበን፣ የዳዋ፣ አፍዴር፣ የሸበሌ፣ የነጎብ፣ የቆራሂ የዶሎ፣ የኤረር እና የጃረር ዞኖች ከ 200 ሚ.ሜ ያነሰ ዝናብ ከ25 ለነሱ ቀናት ተመዝግቦል:: በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ የነበሩት የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከ101-500 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ21-46 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡

በሌላ በኩል የበጋ ዝናብ ተጠቃሚ ባልሆኑት አከባቢዎች ማለትም በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በምስራቅና በመካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የዋግህምራ ዞን፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ የማሂ፣ ጋቢ፣ ሃዉሲ እና ሃሪ ዞኖች ላይ ከ61-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ7-25 ቀናት ያህል ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 1 እና 2) ፡፡


ባለፈዉ በጋ የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሊ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኙ ሲሆን ፤ከሶማሌ ክልል የሊበን፣ የዳዋ፣ አፍዴር፣ የሸበል፣ የነጎብ፣ የቆራሂ የዶሎ፣ የኤረር እና የጃረር ዞኖች፤ መደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3)፡፡ በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ የነበሩት የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የደቡብ ምስራቅ እና ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኙዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3)፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ብዛት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ከኖቬምበር 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባሳለፍነው የኦክቶበር ወር 2024 በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት በተለይም በቦረናና ጉጂ ዞኖች ለሚካሄደው መጠነኛ የሰብል ልማት የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ አጋማሽ በሚገኙ የሀገራችን አካባቢዎች ተጨማሪ እርጥበት ለሚያስፈልጋቸውና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ የመኸር ጊዜ ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በዚህ ወቅት የተገኘው እርጥበት በተለይም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር የጎላ ሚና ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት ዘግይተው ተዘርተው እድገታቸውን ላልጨረሱና ከመስከረም ወር መጀመሪያ ጀምሮ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት ለተዘሩ እንደ ሽንብራና ጓያ ላሉ የጥራጥሬ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች እንዲሁም በአረንጓዴ አሻራ ለተተከሉ ተክሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር አዎንታዊ ጎን ነበረው፡፡ በአንጻሩ ግን በተለይም በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ እንዲሁም በአንዳንድ የመካከለኛው የሀገራችን አካባቢዎች የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው፡፡

ባሳለፍነው የኖቬምበር ወር በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ተስተውሏል። ይህም ሁኔታ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በሌላም በኩል በምራብ፣ በሰሜን ምራብ እና በደቡብ ምራብ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የነበረው እርጥበት ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍርፍሬ ተከሎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች ጠቀሜታ የነበረው ቢሆንም፤ በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የመካከለኛዉ፣ የምስራቅ እና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

አልፎ አልፎ የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በተለይም በደረሱ እና በመሰብሰብ ላይ በሚገኙ ሰብሎች ላይ በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው፡፡ በአንጻሩም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ፣ የደቡብ ምዕራብ እና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት በተለይም በደጋማው አካባቢ በቦረናና ጉጂ ዞኖች ለተዘሩ ሰብሎች ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ሲሆን በአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልና የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማችት ገንቢ ሚና ነበረው (ካርታ 4ሀ እና 4ለ) ፡፡




ካርታ4ሀ፡በኦክቶበር ወር የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ4ለ፡በኖቬምበር ወር የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ሁለት የበጋ ወራት በአባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢ ሸበል፣ ኦጋዴን፣ በላይኛው እና በመካከለኛው አዋሽ፣ እንዲሁም በመካከለኛው እና በታችኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት መጠን በኦክቶበር ወር አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም አብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ መካከለኛው እና የታችኛው አባይ፣ ስምጥ ሸለቆ እና ጥቂት የላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በኖቬምበር ወር የነበረው እርጥበት ምንም እንኳን በስርጭት ረገድ የተስፋፋ ቢሆንም በመጠን ረገድ ግን በተለይም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የቀነሰ ነበር፡፡ የበጋ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የገናሌ ዳዋ፣ ኦሞ ጊቤ፣ በመካከለኛው እና በታችኛ ስምጥ ሸለቆ፣ ላይኛው እና መካከለኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች እርጥበት የነበራቸው ሲሆን በተጨማሪም በአብዛኛው አባይ፣ በላይኛው እና መካከለኛው አዋሽ እንዲሁም በጥቂት መካከለኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በአጠቃላይ በዚህ የበጋ ወቅት አጋማሽ በኦክቶበር መጨረሻ ከነበረው ከፍተኛ ዝናብ ጋር ተያይዞ በመካከለኛ ኦሞ ጊቤ በኮንታ ልዩ ዞን ከተከሰተው የመሬት መንሸራተት ካስከተለው አደጋ በስተቀር በአብዛኛው ተፋሰሶች ላይ የተገኘው እርጥበት ግድቦች ከረዥም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ውሃ መጠን እንዲኖራቸው ያስቻለ ነበር( ካርታ 5 ሀ እና ለ)፡፡



ካርታ5ሀ፡በኦክቶበር ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን





ካርታ 5ለ፡በኖቬምበር ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ ኖቬምበር 30/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ሁለት የበጋ ወራቶች ላይ ለወባ መፈጠርና መስፋፋት ምቹ የአየር ሁኔታ በተለያዩ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ተስተውሏል፡፡ በተለይም በምዕራብ ትግራይ፣ ሰሜን ጎንደር፣ ምዕራብ ጎንደር፣ ማዕከላዊ ጎንደር፣ ምሥራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሊ አባቦራ፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሁሉም የጉጂና የቦረና ዞኖች፣ ምሥራቅ ሸዋ፣ ሁለቱም የባሌ ዞኖች፤ ኢታንግ፣ አኝዋክ፣ ማጃንግ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ምዕራብ ኦሞ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ወላይታ፣ ከንባታ፣ ሀድያ፣ ስለጤ፣ አሌ፣ ኮንሶ፣ ደራሼ፣ ዳዋ እና ሊበን ዞኖች ባሳለፍናቸው ወሮች ላይ ለወባ ስርጭት ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች ነበሩ (ካርታ 6ሀ እና ለ)።



ካርታ 6ሀ. በኦክቶበር ወር ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች





ካርታ 6ለ በኖቨምበር ወር ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች


በሌላ በኩል ባለፉት ወራቶች የነበረው የአየር ሁኔታ ተፅዕኖ ከሰዎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ አኳያ ከፍተኛ የሆነ አስጨናቂ የአየር ሁኔታ ባይከሰትም አልፎ አልፎ በጥቂት የአፋር፣ ጋምቤላ እና ደቡባዊ የሶማሌ ዝቅተኛ ቦታዎች ላይ ጠንከር ያለ አስጨናቂ (Heat strees) አየር ሁኔታ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ ተከስተው እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉብ (ካርታ 6 ሐ እና መ)።



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et



ካርታ 6ሐ. በኦክቶበር ለሰው ልጅ ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች




ካርታ 6መ. በኖቬምበር ወር ለሰውል ልጅ ለመኖር ምቹ የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2024 እስከ ጃንዋሪ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የዲሴምበር እና የጃንዋሪ ወራቶች በአብዛኛው የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ ገፅታዎች የሆኑት ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝኑበት ከመሆኑም በተጨማሪ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በተለይም ለውርጭ ተጋላጭ በሆኑ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሚያይልበት ጊዜ ነው። በአንፃሩ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ እንዲሁም ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞም በጥቂት የሰሜን ምሥራቅ አማራ ቦታዎች ላይ ዝናብ ይስተዋላል።

በመጪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ አብዛኛው ክፍል የባህር ወለል ቅዝቃዜዉ እየቀነሰ እንደሚገኝ የተተነበየ ሲሆን፤ በቀሪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት እ.ኤ.አ 2024-25 (ዲሴምበር እና ጃንዋሪ) ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት ከታህሳስ ወር በኋላ ቀስ በቀስ ቅዝቃዜዉ ወደ (Enso-neutral) የመሆን እድሉ እስከ 52% ሊደርስ እንደሚችልና እንዲሁም የህንድ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ(Neutral_IOD) ሆኖ እንደሚቀጥል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በመሆኑም በቀጣዮቹ ሁለት የበጋ ወራቶች በአብዛኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የበጋው ደረቅ፤ ጸሀያማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ እንደሚዘወተርባቸው የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በተለይም በምስራቅ፤ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ ከ 5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሊሆን እንደሚችልና አልፎ አልፎም ውርጭ የማስከተል አቅም ሊኖረው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በሌላ በኩል በጥቂት የደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚህም ሌላ የበጋው ወቅት ማብቂያ አካባቢ ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ በምሥራቅ አማራ የሚገኙ የሰሜን ሸዋ፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች እንዲሁም ደቡባዊ የአፋር ዞኖች ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል።

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2024 እስከ ጃንዋሪ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ ሁለት የበጋ ወራት (ዲሴምበር እና ጃንዋሪ) 2024_25 በአብዛኛው የበጋው ደረቅ የእረጥበት ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን ሁኔታ የደረሱ ሰብሎች ለመሰብሰብና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በተለይም በጥቂት የምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ሊኖር የሚችለው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት ጥምር ግብርና ለሚያካሂዱ ለደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን በተጨማሪም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩል በምስራቅ፤ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን አልፎ አልፎ ከ 5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆንና፤ ይህም ሁነታ በተወሰኑ ዕጽዋቶች ላይ እና ሰብሎች አሉታዊ ተጽዕኖ የማስከተል አቅም ሊኖረው ይችላል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በአንፃሩም በጃንዋሪ ወር የሚገኘው እርጥበት የበልግ ወቅት የእርሻ እንቅስቃሴን ቀድመው ለሚጀምሩት አካባቢዎች የአፈር ውስጥ እርጥበትን ስለሚያሻሽል የማሳ ዝግጅት ለማደርግም ሆነ ዘር ለመዝራት አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2024 እስከ ጃንዋሪ 31/2025_የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥት የዲሴምር እና የጃንዋሪ መጪ ሁለት ወራት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚያመዝን የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል የበጋ እርጥበት ተጠቃሚ የሆኑ የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ተፋሰሶች በተለይም በመካከለኛው እና በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ በመካከለኛው ዋቤ ሸበሌ፣ በላይኛው እና መካከለኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች በጣም መጠነኛ እርጥበት ያገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን የወኃ ሀብትን ከማማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን የሚመለከታቸወ አካላት የሚገኘው እርጥበት በተገቢ ሁኔታ በማሰባሰብና ክብከነት እና ከብክለት በመጠበቅ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ይመከራል፡፡ በአንጻሩ ግን አብዛኛው አዋሽ፣ ተከዜ፣ አባይ፣ አፋር ደናክል፣ ኦጋዴን፣ አባይ፣ የላይኛው ስምጥ ሸለቆ እና ኦሞ ጊቤ ተፋሰሶች ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል፡፡

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1/2024 እስከ ጃንዋሪ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀሪዎቹ ሁለት የበጋ ወራቶች ላይ ምቹ የአየር ሁኔታ የመፈጠር እድሉ ያነሰ ቢሆንም የተፅዕኖው ሁኔታ ግን ቀጣይነት ይኖረዋል። ይህም ባሳለፍናቸው ሁለት የበጋ ወራቶቸ ላይ የነበረው ምቹ ሁኔታ ለወባ መፈጠርና መስፋፋት ተፅዕኖው በቀጣዮቹ ወራቶች ላይም ቀጣይነት እንደሚኖረው ይጠበቃል። በዚሁ መሠረት የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ እንዲሁም የምዕራብ ኦሮሚያ ሁሉም ዞኖች እና የጉጂና ቦረና ዞኖች፣ የዳዋና የሊበን ዞኖች በቀጣዮች ቀሪ የበጋ ወራቶች ላይ ለወባ በሽታ ተጋላጭ እንደሚሆኑ ይጠበቃል። ስለሆነም ህበረተሰቡና የሚመለከተው አካል ይህን ተፅዕኖ ለመከላከለና ለመቆጣጠር የሚያስችል የቅድመ መከላከል ዝግጅት ማከናውን ያስፈልጋል።



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል ቀሪዎቹ የበጋ ወራቶች ከሰው ልጅ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ አንፃር በተወሰኑ የሀገራችን ሰሜንና መካከለኛው ከፍተኛ ቦታዎች ላይ የጠዋትና የማታው ቅዝቃዜ የሚስተዋልባቸው ከመሆኑ በስተቀር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል ላይ ምቹ የሆነ የአየር ሁኔታ እንደሚሆን ይጠበቃል። አስጨናቂ የሙቀት ሁኔታው በቀጣዮቹ ሁለት የበጋ ቀሪ ወራት እንደሚቀንስ ይጠበቃል።



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et